ፋ/ኮ-74
22-02-09

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር 3-5ኮ0/179/09
Ref. No
ቀን 21 ጥቅምት 2009
Date

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ
በያለበት፣

ጉዳዩ ፡- የንግድ ድርጅታቸውን ከዘጉ ግብር ከፋዮች በሽያጭ የሚወገዱ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የግዥ ማስረጃ ይመለከታል፣

የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ አወጋገድ ትግበራ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 114/2008 በባለስልጣኑ ወጥቶ በስራ ላይ እንዲውል መደረግ ይታወቃል። በዚህ መመሪያ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የሚወገድባቸዉ ምክንያቶች በተገለጸበት አንቀጽ 4

1. ተጠቃሚዉ የንግድ ስራዉን በጊዜያዊነት ሲያቆም ወይም ድርጅቱን ሙሉ በሙሉ ሲዘጋ ፣
2. መሳሪያዉ በሌላ ሲተካ ወይም ሲቀየር እና፤
3. መሳሪያዉ ሲበላሽ ወይም መለዋወጫ ሊገኝለት የማይችል ወይም የማይሰራ ሆኖ ሲገኝ እንደሆነ በግልጽ ሰፍሯል።

ከላይ የተገለጹት ምክንያቶች ሲያጋጥሙ በመሣሪያው ተጠቃሚ ምርጫ የሚወገድባቸዉ ሁኔታዎችንም በዚሁ መመሪያ አንቀጽ 5 የተገለጸ ሲሆን፣

1. መሳሪያዎቹን ለአቅራቢዉ ወይም ለአገልግሎት ማእከሉ በአደራ በማስቀመጥ ለሌላ ተጠቃሚ በሽያጭ ወይም በስጦታ ማስተላለፍ ወይም
2. ለአቅራቢዉ ወይም ለአገልግሎት ማእከሉ በገበያዉ ዋጋ በመሸጥ ወይም
3. በሽያጭ ሊወገዱ የማይችሉ ወይም የእርጅና ጊዜያቸዉን ያጠናቀቁ ወይም በሌላ በማናቸዉም ምክንያት ያልተወገዱትን መሳሪያዎች ያለምንም ዋጋ ለባለስልጣኑ ማስረከብ እንደሆነ ተመላክቷል።

ነገር ግን በአንቀጽ 5 (1 እና 2 ) በተጠቀሰው መሰረት ለግብር ከፋዮች በተለይ አቅራቢዎች ወይም አገልግሎት ማእከሉ የሚወገዱ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎችን የንግድ ስራቸዉን ካቋረጡ ወይም ከዘጉ ግብር ከፋዮች በሽያጭ የሚወገዱ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ግዥ በሚፈጽሙበት ጊዜ ለፈጸሙት ክፍያ ደረሰኝ የማያገኙ በመሆኑ በወጭነት የሚመዘግቡት ቢታክስ ባለስልጣኑ ፅውቅ እና

ለዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!

ስልክ ቁ / Tel. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ / Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ. / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

ተቀባይነት ያለዉ ማስረጃ የሚያስፈልጋቸዉ በመሆኑ የሽያጭ ደረሰኝ ሊቀርብላቸዉ ላልቻሉ ግብይቶች ግዥ ስለመፈጸሙ በግዥዉ ተዘጋጅቶ በወጪ ማስረጃነት እንዲቀርብ የደረሰኝ ህትመት ፈቃድ አሰጣጥ፣ አያያዝ፣ አጠቃቀም፣ አወጋገድ እና ቁጥጥር በመመሪያ ቁጥር 110/2008 አንቀጽ 12/1 መሰረት የግዥ ማረጋገጫ ደረሰኝ (Purchcse Voucher ) መጠቀም እንዲችሉ እንዲፈቀድ ተጠይቋል::

በዚህ መሠረት የሚወጣዉ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች በመመሪያ አንቀጽ 12/1 መሰረት የግዥ ማረጋገጫ ደረሰኝ (Purchcse Voucher ) መጠቀም እንዲችሉ ከተዘረዘሩት ውስጥ የማይገኝ በመሆኑ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ደረሰኝ የማይገኝላቸው ግብይቶች በመሆናቸው በግዥው የሚሰጥ የግዥ ማረጋገጫ ደረሰኝ /Purchase Voucher/ በመጠቀም ግብይት የሚፈጸምባቸው ተጨማሪ ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ዝርዝር ባለስልጣኑ በሰርኩላር ሊያስታውቅ እንደሚችል በተገለጸው መሠረት የሚወጣዉ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያዎች የንግድ ስራቸዉን ካቋረጡ ወይም ከዘጉ ግብር ከፋዮች ግዢ ሲፈጸም ተፈጻሚ እንዲደረግ ተፈቅዷል::

ስለዚህ በዚህ አግባብ ተፈጻሚ እንዲደረግ የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች እና ሠራተኞች እንዲያውቁትና በዚህ መሠረት መፈጸሙን ድጋፍና ክትትል እንዲደረግ እየገለጽኩ፣ በመመሪያው መሠረት የሚወጣውን የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያ የሚገዙ ግብይቱን ስለመፈፀማቸው በግዥ ማረጋገጫ ደረሰኙ /Purchase Voucher/ ላይ የሻጩን ስም፣ አድራሻ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥሩን በመመዝገብ የሻጭ ፊርማ እንዲሰፍር ተደርጎ እንዲከናወን መደረግ እንዳለበት እንዲያውቁት በአክብሮት እንዲገለጽላቸው አሳስባለሁ::

ከሰላምታ ጋር

ደስታ በዛብህ
ም/ዋና ዳይሬክተር
የሀገር ውስጥ ታክስ ፍኖተራም ልማት ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ

ግልባጭ፡
- ኢሞና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለሕግ ማስከበር ዘርፍ
- ለአዲስ አበባ ሀገር ውስጥ ታክስ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለፌደራል አገር ውስጥ ታክስ ጉዳይ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለክልሎች ድጋፍ ትብብር ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ አዲት አሠራር ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለግብር አወሳሰንና አሰባሰብ አሠራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለኢንቨስትጌሽን አዲት ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለተምሀርትና ግንኙነት ዳይሬክቶሬት

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን